**በግጭት፣ በቀውስ ወይም ከፍተኛ ውድመት በሚያጋጥምበት ወቅት፣ ከቤተመጻህፍትና ከእነርሱም ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን በተመለከተ መኖር ስለሚገባው ንቁና ገንቢ ተሳትፎ የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን መሪ ሃሳብ**

የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ከፍተኛ አመራር አካል እ.ኤ.አ. በኦገስት 19 ቀን 2011 ባካሄደው ስብሰባ ከፍተኛ የተፈጥሮ ውድመትን በመቀነስና ግጭት ወይም ቀውስ በሚያጋጥምበት ወቅት የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እና አባላቱ ሊከተሉት ስለሚገባ **ንቁና ገንቢ ተሳትፎ ረቂቅ መርህ** እንዲያዘጋጅ አንድ አማካሪ ቡድን አቋቁሟል። ጥናቱ የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ሄይቲ በምትባለው ሃገር የመልሶ ግንባታ ጥረት ውስጥ ያደረገውን ንቁና ገንቢ ተሳትፎና ፌዴሬሽኑ ተዋዋይ ከሆነባቸው ዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች ጋር ተጣቅሶ እንዲካሄድ ፍላጎት የተንፀባረቀበት ነበር። መርሆዎቹ ፌዴሬሽኑ ከ2011 እስከ 2012 በሚዘልቀው ፕሮግራሙ ውስጥ ያሰፈራቸውና “የባህላዊ ቅርሶች ውድመት መልሶ ግንባታ ፕሮግራም” በሚል ርዕስ ስር “ባህል የሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎት መገለጫ ነው፤ ማህበረሰቦች በባህላዊ ቅርሳቸው አማካይነት ይበለፅጋሉ፤ እርሱን ባጡም ጊዜ ይጠፋሉ” የሚለው ቁልፍ የተነሳሽነት ሃሳብ አንድ አካል ናቸው።

በቅርቡ በሶሪያና በማሊ በተካሄደው ብጥብጥ እንዲሁም በሄይቲ በተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥና በጃፓን ውስጥ የመሬት መንቀጥቀጥን ተከትሎ ባጋጠመው የሱናሚ አደጋ መነሻነት በባህላዊ ቅርሶች ላይ የደረሰው ከፍ ያለ ውድመት የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽንን በጥልቅ ያሳስበዋል። መርሁ ግንዛቤዎችን በማሳደግና ድንገተኛ አደጋዎችን ለመቋቋም የሚያስችል ብቃትን በማዳበር ባህላዊ ቅርሶች በአግባቡ እንዲጠበቁና ተገቢውን አክብሮት እንዲያገኙ ያበረታታል። እንዲሁም በዩኔስኮ፣ በቤተመጻህፍት፣ በቤተመዛግብት፣ በሙዚየሞች፣ የቅርስ ስፍራዎችና ህንጻዎች እንዲጠበቁ በሚሰሩ ቡድኖች እና በዓለምአቀፍ የቅርስ ጥበቃ ኮሚቴ አማካይነት በሚካሄዱ የቅርስ ጥበቃ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖርና የተጠናከረ ትብብር እንዲኖር ያበረታታል።

**የንቁና ገንቢ ተሳትፎ መርህ** የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እና አባላቱ አደጋ ሊከሰትባቸው የሚችሉ ቦታዎችን እንዴት በቅርበት መከታተል እንደሚችሉና እንዲሁም ድንገተኛ አደጋዎችን በመከላከል ዘመቻ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት እንዴት መሰለፍ እና ድንገተኛ አደጋን ስለመከላከል ማስተማር እንዴት እንደሚችሉ ምክር ይሰጣል። ድንገተኛ አደጋ በሚያጋጥም ወቅት **የንቁና ገንቢ ተሳትፎ መርህ** የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴውን የሚመራ ሲሆን በተጨማሪም የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እና አባላቱ በፌዴሬሽኑ ስትራቴጂያዊ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው በመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴው ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ተገቢውን ምክር ይሰጣል። እንዲሁም ግጭት ከመከሰቱም በፊት ሆነ በመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴው ውስጥ የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን እና አባላቱ መካፈል ይገባቸው እንደሆን ለመወሰን የሚረዳ መስፈርት የሚያዘጋጅ ሲሆን መካፈል ይገባቸዋል ከተባለም በምን ደረጃና ሁኔታ እንደሚካፈሉ መምሪያ ይሰጣል። መርሁ የአለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ጣልቃ ስለሚገባበት ሁኔታ፣ ስለሚመራበት መርህ፣ የተሳትፎውን ደረጃ እና የእርዳታ ፍላጎቱን መጠን ለመመዘንና ለመወሰን የሚያስችለውን ዘዴ በዝርዝር ያስቀምጣል።